DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

Office of Family and Public Engagement

# ለቻንስለር የወላጅ አማካሪ ምርጫ ማመልከቻ

የቻንስለር የወላጅ አማካሪ ቡድን (የወላጅ አማካሪ ቡድን) የወላጅ መሪዎች የድርጅቱ ፖሊሲዎች እንዴት ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች ላይ ተፅእኖ እንደሚኖራቸው ለቻንስለሩ በቀጥታ የሚያሳውቁበት ዘዴ ሆኖ ያገለግላል። በ 2017-2018 የትምህርት ዓመት የወላጅ አማካሪ ቡድኑ የሚከተሉትን ጨምሮ በበርካታ ርእሶች ላይ ይወያያል፤ መካከለኛ ትምህርት ቤቶቻችን ላይ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ፤ የበጀት ሂደት ላይ ግልጽነትን ማሻሻል፤ ተማሪዎችን ለኮሌጅ እና ለስራ ማዘጋጀት፤ በማህበራዊ/ስሜታዎ ትምህርት እና “በእውነተኛው ዓለም” ተጠቃሚነት የማጎልበት ትምህርቶች በኩል የልጁን ሁለንተና ማጎልበት፤

የወላጅ አማካሪ ቡድኑ በዲሲፒኤስ (DCPS) ውስጥ ቢያንስ አንድ ልጅ ያላቸው እና (ወይም ደግሞ ልጃቸውን በቅርቡ ዲሲፒኤስ (DCPS) ለማስገባት የተዘጋጁ ወላጆች) የዲሲፒኤስ (DCPS) ማህበረሰብ የተለያዩ ማህበረሰቦች ድብልቅ መሆኑን የሚያንጸባርቁ የዲሲ ወላጆችን ያካተተ ነው። ስብሰባዎች ቻንስለሩን፤ አባላትን እና ቁልፍ የሆኑ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞችን ያካትታሉ። የወላጅ አማካሪ ቡድን ማመልከቻን የሚገመግመው ቦርድ የከተማችንን እና የትምህርት ቤት ማህበረሰባችንን የብዙ ማህበረሰቦች ድብልቅ መሆኑን ሊያንጸባርቅ የሚችል የወላጆች ቡድን እየፈለገ ነው። ዕጩዎች የሚገመገቡት ከዲሲፒኤስ ጋር ያላቸውን ጠንካራ ግንኙነት በማሳየት ችሎታቸው፤ ለፍትህ እና የተለያዩ መሆንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሚኖራቸው የበሰለ አስተሳሰብ፤ እንዲሁም የዲሲፒኤስ ውሳኔዎችን በክልል አቀፍ ደረጃ ስለሚኖራቸው ተፅዕኖ በሚኖራቸው የበሰለ አስተሳሰብ ይሆናል።

**የአመልካች መረጃ (ይህ መረጃ በዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኛ ብቻ የሚታይ ነው)**
(በእጅ የሚጽፉ ከሆነ አባክዎ በጥቁር ወይም ሰመያዊ ቀለም ይጻፉ)

| | | |
|---|---|---|
| ማዕረግ፤ | ስም፤ | የቤተሰብ መጠሪያ ስም፤ |
| ስልክ ቁጥር፤ | | ኢሜይል፤ |
| መኖሪያ አድራሻ፤ | | |
| አካባቢ (ለምሳሌ ሻው (Shaw)፤ ዲንዉድ (Deanwood) ወዘተ…) | | ዋርድ (Ward)፤ |
| ቋንቋ፤ | | ሙያ፤ |
| የልጁ/ጆቹ ትምህርት ቤት/ቶች (ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉንም ይጻፉ)፤ | | የልጁ/ጆቹ የክፍል ደረጃ/ዎች (ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉንም ይጻፉ)፤ |

**በጽሁፍ መልስ የሚሰጣቸው ጥያቄዎች (እባክዎ ለሁሉም መልስ ይስጡ፤ ከ 1እስከ 2 ምዕራፍ ለእያንዳንዱ):**
እባክዎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሌላ ወረቀት ላይ ይመልሱ። እባክዎ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ስምዎ መኖሩን እና ከላይ የሚገኘው የአመልካች መረጃ መካተቱን ያረጋግጡ። እያንዳንዱን ጥያቄ ከ 1 እስከ 2 ምዕራፎች መመለስ መቻል አለብዎት።

1) በቻንስለር የወላጅ አማካሪ ቡድን ውስጥ ለማገልገል ስላለዎት ፍላጎት እና ምን አስተዋጽዖ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ያብራሩ

2) እንደ የወላጅ አማካሪ ቡድን አባልነት ሊያተኩሩባቸው የሚፈልጓቸው ሶስት ዋና ዋና በክልል ደረጃ ያሉ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ምንድናቸው እናም ለምን?

3) በዲሲፒኤስ (DCPS) ውስጥ ፍትህ ማለት እያንዳንዱ ተማሪ ለስኬታማነት የሚያስፈልጉት ነገሮች ያሉት መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ዲሲፒኢአስ (DCPS) በትምህርት ክፍሎቹ፤ ትምህርት ቤቶቹ እና ማህበረሰቦቹ ውስጥ ፍትህን እና ጥራትን እንዴት የበለጠ ሊያሳድግ እንደሚችል ያብራሩ።

4) በአማካሪ ቡድን ስብሰባ ዲሲፒኤስ (DCPS) ተግባራዊ ስለሚያደርገው አዲስ መርሃ-ግብር ሰሙ። ቻንስለሩ ይህንን መረጃ አማካሪ ቡድኑን ለትምህርት ቤት ማህበረሰቦች እንዲያካፍል፤ ከሌሎች ወላጆች ምላሽ እንዲሰበስብ እና በሚቀጥለው ስብሰባ መልሶ ሪፖርት እንዲያደርግ ጠየቀ። ይህንን መረጃ ለማካፈል እና ከመሰሎችዎ ምላሽ ለመሰብሰብ ዕቅድዎ ምንድነው?

**ማረጋገጫዎች ፤**

ይህንን ማመልከቻ በማስገባት ለቻንስለር የወላጅ አማካሪ ቡድን ለመመረጥ እና የሚከተሉትን መስፈርቶች የማሟላ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

- የዲሲ (District of Columbia) ነዋሪ ነኝ፤
- ልጄ/ጆቼ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው/ተማሪዎች ናቸው (ወይም የወደፊት የዲሲፒኤስ (DCPS) ተማሪ ወላጅ ነኝ)፤
- በ __________ከ 5:30 እስከ 8 ፒ.ኤም. የሚደረገውን የመጀመሪያ የወላጅ አማካሪ ስብሰባ መካፈል እችላለሁ፤ እንዲሁም በየወሩ የሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ለመሳተፍ እጥራለሁ፤ እና
- በወላጅ አማካሪ ስብሰባ ላይ መካፈል ክፍያ ወይም ላጠፋሁት ወጪ ማካካሻ እንደሌለው አውቃለሁ።ም

**ማስታወሻ፤ የማመልከቻው የመጨረሻ ቀን ዓርብ ጁን 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በ 11:59 ፒ.ኤም ነው።**

ወላጆች ማመልከቻቸውን Parents can submit the application by:

- በ http://bit.ly/dcpsparentcabinet የኢንተርኔት ላይ ማመልከቻ በመሙላት፤ ወይም
- ይህንን የተሞላ የማመልከቻ ዶክመንት በ ofpe.info@dc.gov ኢሜይል በመላክ ወይም
- ይህንን የተሞላ የማመልከቻ ዶክመንት ወደ፤
  DCPS Office of Family and Public Engagement
  1200 First St. NE. Floor 12
  Washington, DC 20001
  በመላክ ማመልከት ይችላሉ።

በሰዓቱ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በፖስታ የሚላኩ ማመልከቻዎች ከ ዕሮብ ጁን 28 ቀን 2017 ዓ.ም. በፊት ፖስታ ቤት መግባት አለባቸው።

ሁሉም አመልካቾች መልስ የሚሰጣቸው ሲሆን ለቦታው የተመረጡ ወላጆች በ ጁላይ 28 ቀን 2017 ማሳሰቢያ ይደርሳቸዋል።